# <u>ሣሙኤል ዓለማየሁ</u>

አምስት ዓመታት ሳሙኤል ተኛ
ሞት አደረገው ምርኮኛ
በስጋ የለ አይነካ አይዳሰስ
ገነት ነው አሉ የደግ ሰው ነፍስ ፡፡

ቁም ነገር ፍቅሩ አብሮን አለ
ትኩስ ነው እንዳየለ
ትዝታ ሳቁ ጨዋታው
አካሄድ ቁመናው መላ ለዛው
ትልቅ ሰው ጀግና የማንተካው
ለጓዶቹና ቤተሰብ ሁሉ ፋና ሚያበራ
ትሁት አዋቂ የማይኩራራ
ተመዝግቧል መልካምነትህ
ሀገርና ሕዝብ ከልብ መውደድህ
ሁሉን ሚረታ ያ ሞት ሆነና
ዝም ቁጭ አልን እንደዋዛ
ናፍቆትህ አርጎን ፈዛዛ፡፡

አንድ ሁለት ሶስት
አራት አምስት ዓመታት
የሣሙኤል ዜና ዕረፍት
ያለጊዜው መቀጨት፡፡

ሞት ዓይኖቹ ዕውር
ደግ ደጉን የማይሰውር
ለሀገር ለወገን ተቆርቋሪ
ስመ ጥሩ ሥራው አኩሪ
ብሎ የማይተው የማይሳሳ
ጀግና ጀግናውን ድል የሚነሳ
አመጣጡ እንግዳ

እንዳንደፍን ቀዳዳ
ተንኮለኛ  ቀማኛ ሌባ
ሀዘኑ ከባድ ሥራው ገለባ፡፡

አምስት ዓመታት ሣሙዔል ተኛ
ሞት አደረገው ምርኮኛ
በስጋ የለ አይነካ አይዳሰስ ፡፡
ገነት ነው አሉ የደግ ሰው ነፍስ ፡፡
ዓመታት መቁጠር ከሆነ ዕጣችን
ተደላድለህ ቆይ ኑር በልባችን ፡፡

ከሚናፍቁት ቤተሰቦቹ